# ካለፈው የቀጠለ: -

## ካለፈው የቀጠለ: -

<u>በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ</u>
<u>ዕብራውያን 12 (Hebrews)</u>
<u>3፤ በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ፥ ከኃጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ መቃወም የጸናውን አስቡ።</u>

2ኛ ቆሮንቶስ 5
1፤ ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፥ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለንና።
2፤ በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃትታለንና፥
3፤ ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና ለብሰን ራቁታችንን አንገኝም።
4፤ በእውነትም የሚሞተው በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ ልንገፈፍ የማንወድ ስለ ሆነ፥ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብዶን እንቃትታለን።
#የለበስነውን ስጋ ፈራሽ ድንኳን መሆኑን የእግ/ር ቃል ይነግረናል
ዕብራውያን 12
1-2፤ እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፥ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።
#የእምነት አባቶቻችን የተሰጠውን ተስፋ ባያገኙም ከሩቅ እያዩት በእምነታቸው የፀኑ ነበሩ ፣ እኛ ግን ተስፋችንን ኢየሱስን አግኝተነዋል ዛሬ እርሱን እያየን ወደ ፊት እንድንገሰግስ ይመክረናል።
በነፍስ መዛል ማለት: -
እምነታችን ፣ ተስፋችን፣ የአምልኮ ህይወት መድከም ማለት ነው።

ነፍስ ከእግዚ/ር ጋር የምንገናኝበት የማንነታችን ክፍል ነው፣ ስለዚህ የነፍስ መዛል ከእግዚ/ር ጋር ያለንን ግንኙነት ያበላሻል።
# ዛሬ የከበበን ምንድን ነው? ሀጢያት?
የዕብራውያን ፀሀፊ ግን
1, የሚከበንን ሀጢያት እና ሁኔታዎች ሳይሆን ፣ እንደደመና ምስክር የሆኑንን የእምነት አባቶችን እንመልከት።
2ኛ, የእምነታችን ጀማሪ እና ፈፃሚ የሆነውን ጌታን ተመልክተን፣ ሩጫችንን በትዕግስት እንሩጥ።
መዝሙር 103
1፤ ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ አጥንቶቼም ሁሉ፥ የተቀደሰ ስሙን።
2፤ ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ፤
# የዳዊት ነፍስ እንዳታመሰግን ዝላ ነበር ፣ ዳዊት ግን ያበረታት ነበር እግዚአብሔር ያደረገላትን እያሰበች እንድትበረታ የነግራት ነበር።
ዛሬ ነፍሳችን በምን ይሆን የዛለችው?
ለእምነት፣ ለምስጋና፣ ለአምልኮ፣ ለአገልግሎት?
ሉቃስ 1
46፤ ማርያምም እንዲህ አለች፡—
47፤ ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤
48፤ የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤
49፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው።
#ማርያም ነፍሴ አለች ፣ ነፍሳችን የተደረገላትን ስታስብ ትበረታለች፣ ታመሰግናለች
1 ቆሮንቶስ 6 (1 Corinthians)
19-20፤ ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ

እግዚአብሔርን አክብሩ።
#ስጋችን እግዚአብሔርን እንዲያከብር ነፍሳችን መበርታት አለባት።
ነፍሳችን የምትዝልባቸው ሁኔታዎች

1ኛ, በወንጌል (አገልግሎት)

2 ቆሮንቶስ 1÷8 -11
8፤ በእስያ ስለ ደረሰብን መከራችን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ታውቁ ዘንድ እንወዳለንና፤ ስለ ሕይወታችን እንኳ ተስፋ እስክንቆርጥ ድረስ ከዓቅማችን በላይ ያለ ልክ ከብዶብን ነበር፤
2 ቆሮንቶስ 11÷ 22 - 33
27፤ በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ።
ወንጌል፣ አገልግሎት ወይንም ጥሪ ነፍስን ያዝላል ፣ ስለዚህ በአገልግሎት እንዳንደክም መፅናት ይኖርብናል።
ቅዱሳን ዛሬም ለወንጌል ስራ መበርታት እና ወንጌልን መስበክ ይገባናል።
የእግዚአብሔርን ስራ ለመስራት ማንነታችንን አንመልከት ኤርሚያስ ከብላቴንነቱ ጀምሮ በብዙ መከራ ውስጥ እያገለገለ በመፅናቱ በመጨረሻ እግዚአብሔር አሳረፈው።

2ኛ, በእምነታችን ምክንያት

ሐዋ. ሥራ 8÷ 1 - 3

1፤ በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፤ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ።
2፤ በጸሎትም የተጉ ሰዎች እስጢፋኖስን ቀበሩት ታላቅ ልቅሶም አለቀሱለት።
3፤ ሳውል ግን ቤተ ክርስቲያንን ያፈርስ ነበር፤ ወደ ሁሉም ቤት እየገባ ወንዶችንም ሴቶችንም እየጐተተ ወደ ወኅኒ አሳልፎ ይሰጥ ነበር።
3ኛ, <u>የዘገየች ተስፋ ነፍስን ታዝላለች</u>
አብርሀም በተስፋው መዘግየት ነፍሱ ዛለች ወደ አጋርም ገባ።
ዘፍጥረት 16 ÷ 1 - 4

2፤ ሦራም አብራምን፦— እነሆ፥ እንዳልወልድ እግዚአብሔር ዘጋኝ፤ ምናልባት ከእርስዋ በልጅ እታነጽ እንደ ሆነ ወደ እርስዋ ግባ፡ አለችው።
3፤ አብራምም የሦራን ቃል ሰማ። አብራምም በከነዓን ምድር አሥር ዓመት ከተቀመጠ በኋላ፥ የአብራም ሚስት ሦራ ግብፃዊት ባሪያዋን አጋርን ወስዳ ለባልዋ ለአብራም ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው።
4፤ እርሱም ወደ አጋር ገባ፥ አረገዘችም፤ እንዳረገዘችም ባየች ጊዜ እመቤትዋን በዓይንዋ አቃለለች።
4ኛ, በሰይጣን ውጊያ ነፍስ ትዝላለች
1 ነገሥት 19 (1 Kings)
2፤ ኤልዛቤልም፦— ነገ በዚህ ጊዜ ነፍስህን ከእነዚህ እንደ አንዲቱ ነፍስ ባላደርጋት፥ አማልክት ይህን ያድርጉብኝ ይህንም ይጨምሩብኝ፡ ብላ ወደ ኤልያስ መልእክተኛ ላከች።
3፤ ኤልያስም ፈርቶ ተነሣ፥ ነፍሱንም ሊያድን ሄደ፥ በይሁዳም ወዳለው ወደ ቤርሳቤህ መጥቶ ብላቴናውን በዚያ ተወ።
#ታላቁ ነብይ ኤልያስ_ በኤልዛቤል ዛቻ ነፍሱ ዛለ።
ኢዮብ 1 (Job)
9፤ ሰይጣንም ለእግዚአብሔር እንዲህ ብሎ መለሰለት፦— በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራ በከንቱ ነውን?
10፤ እርሱንና ቤቱን በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን? የእጁን ሥራ ባርከህለታል፥ ከብቱም በምድር ላይ በዝቶአል።
4ኛ,በሀጢያት
መዝሙር 106
የእስራኤል ህዝብ በሀጢያታቸው ምክንያት ነፍሳቸው ከሳች ዛለች ......
13፤ ፈጥነውም ሥራውን ረሱ፥ በምክሩም አልታገሡም።
14፤ በምድረ በዳም ምኞትን ተመኙ፥ በበረሃም እግዚአብሔርን ተፈታተኑት።
15፤ የለመኑትንም ሰጣቸው፤ ለነፍሳቸው ግን ክሳትን ላከ።
2 ጴጥሮስ 1 (2 Peter)
4፤ ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት

የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን።
5፤ ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥
6፤ በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፥
7፤ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።
8፤ እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጉአችኋልና፤
በሦስት ነገሮች ነፍሳችን ትፀናለች
1ኛ,ትላንት የተደረገልንን ነገር ስናስብ
2ኛ, እግዚአብሔር የሰጠን በግልም ሆነ በተፈጥሮ ያለንን በረከት ስናስብ።
3ኛ, ተስፋችንን ስናስብ።
ጌታ ይርዳን። አሜን።

Last modified: 12:58 PM